ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ

በሚያዚያ 23 ቀን 2010 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ምን ተይዞ ጉዞ ?

ከአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድት 1966ዓም ጀምሮ እስከ ዛሬ 2010 ዓም ድረስ፤ የአገራችንና የሕዝቦቿ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ ምላሽ ሳያገኝ ቀርቷል። ጥያቄው ሳይመለስ በመቅረቱ ፤ ሕዝባዊው ትግል አሁንም እንደቀጠለ ነው። በነኝኽ 44 ዓመታት በመካሄድ ላይ ባሉት ሕዝባዊ ዐመፆች ምክንያት፤ በሰው ሕይወትም ሆነ በሀገር ሀብት ላይ የደረሰው ጉዳትና ጥፋት በዐሃዝ ሊገመት የሚችል አይሆንም። የሀገር ሀብትና ንብረት ውድመት የቱን ያህል እንደሆነ፤ በትክክል መናገር ያስቸግራል። ያ ሁሉ ኪሳራ ደርሶ ግን ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ፤የፈለገውን ውጤት ሊያስመዘግብ አልቻለም። የትግሉ ጉዞ ተስፋን ሰንቆ ቢጓዝም፤ " **ምን ተይዞ ጉዞ** ? የሚለውን ጥያቄ መነሻ አድርጎ ባለመጓዙ ፤ ጉዞው ሁሉ አቅጣጫ ቢስ ሆነ ቀርቷል። የታሰበውን ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም ።

በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ፤ ከመነሻው ጀምሮ አቅጣጫውን ቀይሶ፤ የመንገዱን መነሻና መድረሻ አመልካች አቅጣጫ አንግቦ ባለመንቀሳቀሱ፤ ለአለፉት አርባ አራት ዓመታት የተካሄደው ሕዝባዊ ትግል የተፈለገውን ወጤት ሊያመጣ አልተቻለውም ። በነኝኽ አርባ አራት ዓመታት ሦስት አባገነን ሥር ዓት ተለዋውጠዋል ። ሦስቱም አመጣጣቸውና የአገዛዝ ስልታቸው በግልብ ሲያዩት፤ የተለያየ ቢመስልም፤ በይዘትና በአካሄድ ግን አንዱ ከሌላው የተሻለ ሳይሆን ፤ አንዲያውም አንደኛው፤ የሌላኛው ያንድ ሳንቲም ግልባጭ ነው ማለት ይቻላል ። ከወያኔ በፊት ስለተፈራርቁት ሁለት አገዛዞች ማንሳት በአሁኑ ወቅት ፋይዳው እብዛም ስለሆነ ፤በዚያ ላይ ማተኮሩ ለጊዜው አንገብጋቢ አይሆንም ። ያን ለታሪክ መተው ይገባል !

ይኽ የቆየ፤ የገነገነ፤ የደለበ፤ የተወሳሰበ፤ የተመሰቃቀለና ስር የሰደደ የሀገራችን ሁለንተናዊ ችግር፤ ግለሰቦች የወንበር ልውውጥ በማድረጋቸው ብቻ መፍተሄ ሊያገኝ አይችልም። አሮጊውን ወንበር በአዲስ ኩርሲ ቢቀያይሩት፤ ስር የሰደደው አምባገንን አገዛዝ እስካልተለወጠ ድረስ፤ በኢትዮጵያ የአዲስ ሥርዓት ጭላንጭል ፈጽሞ አይታይም።

ግልሰቦች መልካም ስብዕና ሊላበሱ ይችላሉ፤ ብሩኅ አዕመሮ ሊታደላቸው ይችል ይሆናል። የትምህርት ዝግጅትና ክኅሎት ሊኖራቸውም ይችል ይሆናል ። የመላዕክትን ቋንቋ በመናገር ለአድማጫቸው መሳጭ፤ አቁነጥናጭና አስደማሚ ንግግር አሰምተው፤ ጣራ ሰንጠቂ ጭብጨባ ሊያተርፉ ይችሉ ይሆናል ። ይኽ ሁሉ ተደምሮ ግን ለሚያገለግሉት አገዛዝ የሕዝብ ግንኙነት ተግባር ከመፈፀም ባሻገር ፤ሕዝብ ለሚጠብቀው አዲስ ለውጥ ቅንጣት ፋይዳ አያመጣም። የሀገራችን ስር የሰደደ ችግር የሚፈታው፤ በግለሰቦች ችሎታና ፈቃድ ብቻ ሳይሆን፤ የሥር ዓት ለውጥ በማምጣትም ጭምር ይሆናል ።የተቋማት ለውጥ ማምጣት ለአዲስ ለውጥ ወሳኝም መሠረታዊም ነው።

በወንበር ላይ እንዲቀመጥ ላደረገው አገዛዝ ዐፈ-ቀላጤ በመሆን፤ ሥርዓቱን ማስቀጠልና ሕዝቡ ለጠየቀው አንገብጋቢና መሠረታዊ ጥያቄ ተገቢውን መልስ ለመስጠት መዘጋጀት የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው ። የወቅቱ የግለሰቦች የሥልጣን ልውውጥ በሕዝቡ ጥያቄ ላይ አንዳችም የሚያመጣው ፋይዳ የለውም። ወቅታዊው የሕዝብ ጥያቄ፤ **ባልተገደበ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ፤ ምርጫ አካሄዶ በራሱ ፈቃድና ውሳኔ የሚስማማውን ሥር ዓተ- መንግሥት አቋቁሞ የነፃነት ዋስትናውን አስከብሮ በሠላም መኖር ነው። ይኽ ደግሞ ፤ በአንድ አምባገነን አገዛዝ ስር በሚለዋወጡ ግለሰቦች ችሎታና ፈቃድ ሊመጣ አይችልም ።**

የትግል መሥዋዕት መክፈልን እንጅ፤ የትግሉን ፍሬ ለማየት ያልተደለው ሕዝብ ፤ ዛሬ በወያኔ አገዛዝ ላይ በሚያከሂደው ዐመጽ ፤ በሥርዓቱ አራማጆች ሰፈር፤ ድንጋጤን አሳድሯል። ውጭ--ነፍስ ፤ ግቢ ነፍስ በመፈጠሩ ምክንያት፤ ጭንቀቱን ለማረጋጋት ሲባል፤ አዲስ ታማኞቻቸውን ቀይረዋል። አይዟችሁ ዕርጉ- ተረጋጉ ለማለት ይጠቅመናል ያሉትን ሰው መሾማቸው፤ በአዲስ ጉልበት ያገለግለናል ብለው የመደቡት ተልካሻ ዘዴ እንጅ ፤ ለሕዝቡ ጥያቄ የሚመልስ ርባና አያመጣም። ነባሩን አገልጋይ፤ በአዲስ ታማኝ ጋሻጃግሬ መቀየር ፤ በሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ማሻሻያ ላይ እርባና አይኖረውም።

" **ሎሌ ባፍላው የአህያ መኾገር ይከላል** " ነውና፤ አዲሱ ተሿሚ ፤ ታማኝነቱን ለማረጋገጥ ያላስፈላጊ ተጨማሪ ኪሎሜትር ርቀት ከመጓዝ ወደ ኋላ አይልም ። በሕዝብ ጥያቄ ላይ አንዳችም ፋይዳ የማያማጣ መሆኑን አስቀድሞ የተረዳው ሕዝብ፤ በአዲሱ የወያኔ ሹም-ሽር ድራማ፤ ተውኔት ሳይደናበር ትግሉን ቀጥሏል ። የንፁሃኑ ደምም እንደጎርፍ እየፈሰሰ ይታያል። ወያኔ ሕዝብ መጨፍጨፉን አላቆመም። ሕዝቡም ዐመፁን አላቋረጠም። ሁኔታውን የሚለውጠው የሥርዓት እንጅ፤ የወያኔ አገልጋዮች ሹም- ሽር አይደለም።

በቄሮና - ፋኖ የትግል መንፈስ ተነሳስቶ መሥዋዕት እየከፈለ የሚታገለው የሀገሪቱ ወጣት ትውልድ፤ ለዚኽ ጉልኅ ማስረጃ ነው ። በሀገሪቱ ላይ በአድራጊ -ፈጣሪ - በፈላጭ - ቆራጭ ፤ አንድ አምባገንን ቡድን በኃይል ተንዘራፍጦ እያለ፤ የሥርዓቱ አገልጋዮች መሸጋሸግ ለውጥ ያመጣል ብሎ መመኘት፤ **"ላም ባልዋለበት ኩበት ለቅማ"** ከመሆን አያልፍም ። የአዲሱ ጠቅላይ ምኒስትር መሰየም ፤ ሕዝባዊው ዐመፅ ከሚያመጣው አደጋ ለመከላከል ታስቦ የተቀናበረ የማዘናጊያና አቅጣጭ አስቀያሬ ዘዴ እንጅ ፤ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ምኅዳር አንዳችም ለውጥ አያመጠም ። የባለሥልጣናቱ ብወዛ ፤ በመሬት ላይ የሚታየውን ሀቅ ሊደብቀው፤ ሊለውጠውና ሊያሻሽለው፤ ፈፅሞ የሚችል አይደለም ። የህዝቡን የዐመፅ እንቅስቃሴ ቀዝቃዛ ውሃ ለመጨመር የተዘየደ የጭንቀት ማለዘቢያ ነው ።

ለሕዝባዊ አመፅ ጥያቄ መስጠት የሚቻለው መሠረታዊ ለውጥ በመምጣ እንደሆነ ሕዝቡ አበክሮ ያምናል ። ጥገናዊ ለውጥ ፤ለመሰረታዊው ሥርዓት ለውጥ በር ሊከፍት ይችላል ብለው የሚመኙ እንደሚኖሩ ባይካድም፤ ከወያኔ የሚሰጣቸው መልስ ግን ፤ " **ሲያምራችሁ ይቅር !** " የሚል ነው ። መሠረታዊ ለውጥ መማጣት የሚቻለው ፤ የሥር ዓት ለውጥ ሲመጣ ብቻ ነው ። ወያኔ ለአገዛዝ ሥርዓቱ መቀጠል ይሟሟታታል እንጅ እንዲሁ በቀላሉ ሥልጥኑን አይለቅም ። ምክንያቱም ፤ያን ካደረገ፤ የሀብት ዝርፊያውን፤ የፖለቲካ ሥልጣንኑ፤ ግድያውን፤ ወታደራዊ ኃይሉን፤ የጸጥታ መዋቅሩን፤ የኢኮኖሚ የበላይነቱን ሁሉ ስለሚገፈፍ፤ ያንን ማጣት አይፈልግም። ወያኔ፤ በሕዝባዊ ዐመፅ ካልተገደደ፤ ወድዶና ፈቅዶ እጁን አይሰጥም ።

ከዚኽም በላይ፤ እስካሁን ለፈፀማቸው የአገር መሸጥ ክኅደት፤ የህዝብ ዕሊቂት ፤ የአገር ሀብት ዝርፊያና ልዩ ልዩ ወንጀሎች ሁሉ ተጠያቂ መሆኑን በሚገባ ስለሚያውቅ፤ በሥልጣኑ ቆይቶ፤ እንደ ቀደምቶቹ ሁሉ፤ ተንኖ ይጠፋታል እንጅ፤ ስሙን እንኳ መጥራት ከሚያንገሸግሸው ፤ ዳግማዊ ሚኒሊክ ካሰሩት ግቢ በፈቃዱ ወድዶ አይወጣም። ከዚኽ ይልቅ፤ አሁን እንደሚያድርገው ኃይለ ማርያምን -በዐብይ፤ ዐብይን፤ በነብይ፤ ነብይን በዘይነባ ዘይነባን በሃዋ ወዘተ.... እያከረባበተ ሌላ ሃያ ሰባት ዓመት ለመቆየት ይሰናዳል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ በኃይል እንጅ በሠላም መግዛት አንችልም ብሎ አምኗልና በኃይል እየቀጠቀጠ በሥልጣን ለመቆየት ያቅዳል። ይመኛል። ለወደፊት ይሳካላታል -አይሳካለትም፤ ሌላ ጥያቄ ነው። እስካሁን ግን ተሳክቶላታል።

የወደፊት ዕቅዱን በተግባር ለማሳካት የሚያስችለው ኃይል ግን ለጊዜው ቢሆን በእጁ ውስጥ አለ ።

**1ኛ.** በሀገሪቱ ወስጥ፤ በአራቱም ማዕዘናት የሰፈረው የመከላከያ ዕዝ/ ኮማንድ፤ ከላይ እስከ ታች በትግራይ ተወላጅ ጦር አለቆች ስር ሆኖ ወያኔ በብቾኝነት ይቆጣጠረዋል ። ይኸ በአክራሪ ብሄረተኞች ቁጥጥር ስር የታጠቀ ሠራዊት፤ የመጀመሪያ ግዳጁም ሆነ ታማኝነቱ፤ የወያኔን አገዛዝ በትጋት ነቅቶ መጠበቅ ስለሆነ ፤ ለጊዜውም ቢሆን ፤ ወያኔዎቹ በማን አለብን ትዕቢት ተማምነው ማነኛውንም የተቃውሞ እንቅስቃሴ በመዳፋቸው ቁጥጥር ስር አድርገው የሚቆጣጠሩት እንደሆነ የተማመናሉ። ቆርጦ የተነሳን ሕዝባዊ ዐመፅ ፤ማነኛውም የተጠቀ የአምባገነን ጦር

እንደማይመከተው ግን ከታሪክ አልተማሩም ። **ወያኔ ፤ መከራ ካልመከረው በስተቀር ፤መካሪ መክሮት የሚሻሻል ድርጅት አይደለም።**

**2ኛ.** የፀጥታውንና የደህንነቱን ዘርፍ በሙሉ የሚቆጣጥሩት አሁንም፤ አክራሪ ብሄርርተኞቹ የትግራይ ተወላጆች ናቸው። በተለይም፤ ከሦስቱም የትግራይ አውራጃዎች ፤ አዳዋ- አክሱምና ሽሬ ፤( አ ዐ ሽ) የተሰባሰቡ ብቻ ሆነው ከሌላው ክፍለ የሚመጣውን ከማሃላቸው እንዳይገባ በጥብቅ የቆጣጠሩታል ።

የሀገሪቱ ፖለቲካ ታሪክ ተከተታዮች፤ የጸጥታውን (ኢንተለጀንሱን) ጉዳይ በግንዛቢያቸው አድርገው ሲገመግሙ፤ ከአሁን በፊት በኢትዮጵያ ከነበሩት መንግሥታት ጋር ሲያነፃጽሩት ፤የወያነ ፀጥታ መሥሪያ ቤት አወቃቀር፤ አደረጃጀትና ሰንሰለት ፤ የሰላዮች ሥልጠናና አመዳደብ፤ አሰራርና ክትትል፤ መርመራና ጭካኔ፤ ከናዜ ጀርመን ጌስታፖ ባለናሰ መልኩ ያወዳደሩታል ።

በቁል ቁልፍ ቦታዎች ያሉት ኃልፊነቶች ከአድዋ፤ አክሱምና ሽሬ ተውላጆች እጅ ቢሆንም ፤ በወሬ አቅባይነት ደረጃ ኅሊናቸውን ለገንዘብ የሸጡ ሌሎች እንደሚተባበሯቸው የታወቀ ነው። ውሻ ላበላው ጭራውን እንደሚቆላ ሁሉ፤ ጥቅመኞች ደግሞ፤ ጊዜ ሲለወጥ ወያኔን ከድተው ለአዲሱ ሁኔታ ሰልፋቸውን እንደሚያሳምሩ ፤ በትግላችን ታሪክ ብዙ ታዝበናል ።

**3ኛ.** የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አዎታሮች፤ የሀብትና ንብረት ማመንጫዎች ባንኮችና ሌሎች የገንዝብ ተቋማት ሳይቀሩ ፤ በወያኔዎቹ ስግብግብ ባለቤትነት ስር ወድቀዋል ። ዘርፊያው፤ ሙስናውና፤ ሽሚያው ሁሉ የሚከናወነው ፤ ባመዛኙ በስግብግቦቹ አክራሪ ብሄረተኞች ቁጥጥር ነው።

ታዲያ፤ ይኽ ወሰንና ገደብ የሌለውን ወታደራዊ ኃይል፤ የፀጥታ መዋቅርና ተዝቆ የማያልቅ ሀብትን ያከማቸ ዘረኛ አምባገነን የገዥ ብድን ( ጉጅለ) በምን አኳኋን ነው ከሥልጣኑ ፈቅዶ በሠላም የለቅቃል ተብሎ የሚታሰብ ? **መልሱ** ፤ በፈቃዱ ሥልጣኑን ለሕዝብ ሊያስረክብ አልተዘጋጀም ነው ።

ይኽንን ማመን ከተቻለ፤ ሥልጣኑ ወድዶም ይሁን ሳይወድ ሊለቅቅ የሚችለው፤ አሁን በመካኼድ ላይ ያለው ሕዝባዊ ዐመፅ ተጥናክሮ ግቡን ሲመታ ነው። በፔርሻ ግዛት፤ በጠንካራ ሠራዊቱ፤ የነዳጅ ሃብቱን በመቆጣጠሩና **ሳቫክ** በመባል የሚታወቀውን ኃይለኛ የመረጃ ተቋም በዕጁ ስር አስገብቶ የነበረው የኢራን ንጉሥ ነገሥት ሻኽ ባህላቢ/ቪ እንኳን ከሕዝባዊው አመፅ ሊተርፍ አልቻለም ። አወዳደቁ የከፋ ሆኖ አልፏል ።

በቅርቡ የኃይለ ማርያም ደሳለኝን ወንበር እንዲቀመጥበት ከወያኔ ፍቃድ የተቸረው ዐብይ አህመድ ዐሊ ፤ ምናልባት ከኃይለማርያ ደሳለኝ የተለየ ግላዊ ስብዕና ሊኖረው ይችል ይሆናል ። ይኽም መሆኑ አያስደንቅም። በዐለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉም ተመሳሳይ ሰብዕና ባኅርይና አስተሳሰብ ሊኖራቸው ስለማይችል፤ ኃይለማርያምና ዐብይ ተመሳሳይ አቅምና ጉልበት ይኖራቸውል ተብሎ አይጠበቅም። ሁለቱ ግን አንድ ተመሳሳይ ስብዕናን ተላብሰዋል። ።

ሁለቱም የራሳቸው ሰዎች አይደሉም። ከወያነ ጉያ የወጡ፤ በወያኔ ጠበል የተጠመቁ ፤ ያደጉ የሠለጠኑ፤ በዘረኝነት ዕምነት የተካኑ፤ ለወያኔ ታማኝነት ቃለ ማሃላ የፈፀሙ፤ ለመኖር ብቻ ሲሉ የኖሩና የሚኖሩ፤ አለቆቻቸው ሲያስነጥሱ ማሃርም ለማቅረብ የሚሽቀዳደሙ፤ ሲጠሯቸው አቤት፤ ሲላኳቸው ወዴት፤ የሚሉ መሆናቸውን ባለፉት ሃያ ሰባት ዐመታት በተግባር አስመስክረዋል። ሲጠሩ አቤት ! ሲላኩ ወዴት ! ሲታዘዙ እሺ ! በማለት እንከን የማይወጣበትን ታማኝነትና ጉድፍ በማይታየበት ታዛዥነት የሚፈጽሙ ስዎች ናቸው፡፡ በመሆኑ፤ በወያኔ ጥብቅ ቁጥጥር ስር ሆኖ፤ ዐብይ አህመድ አሊ፤ የሕዝቡን የመሠረታዊ ለውጥ ጥያቄ ለማስተናገድ ምኞት ቢኖረውም እንኳ፤ ሊያድረግ አይችልም። ወያኔም አይፈቅድለትም።

አዲስ የተሾመው ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው፤ ወያኔ ያዘዘውን ከመፈፀም ውጭ የአክራሪ ዘረኞቹን አቋምና ኣላማ የሚጻረር አንዳችም ጉዳይ ሊያከናውን ዕድል አያገኝም። ልስራ ብሎ ቢሞክርም ፤ መስራት አይችልም። መፈልግና ፍላጎትን

መተርጎም የተለያዩ ስለሆነ፤ ለመስራት ቢሞክርም እንኳ ፤ የወያኔን ሙሉ ፈቃድ ካላገኘ ፤ አንዳችም ጉዳይ አይፈፅምም ። ይኸንን ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ይረዳል። በዚኽም ምክንያት፤ ቢያንስ ቢያንስ የወያኔ- የኢሕአዴግ መዋቅር ፈራርሶ ፤ ሁሉንም ሀገር አቀፍ ፓለቲካዊ ኃይላትን የሚያካትት ምኅዳር ካለመጣ ፤ ለውጥ ይገኛል ብሎ አያምንም። ለዐብይ አህመድ መሹም፤ " **ሹመት ያዳብር !** " አይልም ። **ትንሽ ጊዜ እንስጠው የሚለው ፍሬ-ፈርስኪ አባባል፤ የአዘናጊዎች ተማጽኖ ፤ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት የለውም !**

እንኳንስ አንኳር መንግሥታዊ ተግባራትን ነፃ ሆኖ፤ በራስ አነሳሽነት ማካናወን ይቅርና፤ የግል እንቅስቃሴውና ዉሎ-አዳሩ ሳይቀር፤ በወያኔ የስለላ መርብ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል እንደሚደረግበት የአደባባይ ምሥጢር ነው ። እርሱ ራሱም ቢሆን ይኸ እንደሚደረግበት የሚስተው አይደለም።

እዚኽ ላይ አንድ ሌላ ማስተዋል የሚገባን ጉዳይ ቢኖር፤፤ የዐብይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ መሰየም፤ የምዕራባውያኑ እጅ ሊኖርበት እንደሚችል በግንዛቤ ውስጥ ማስገበትን ይሆናል። በእነርሱ የዳማ ጨዋታ ውስጥ፤ የኢትዮጵያ መረጋጋት ወይም አለመረጋጋት ትልቅ የትኩረታቸው መስህብ መሆኑን ነው፡፡ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ኢትዮጵያ ትልቅ ስትራተጂያዊ ቦታና ሚና እንዳላት ስለሚያውቁ፤ እናም ደግሞ፤ በሕዝቧና በወያኔዎቹ መካከል ያለውን ተቃርኖ በቅርብ ስለሚከታተሉ፤ ህዝባዊው ዐመጽ፤ ወዴት እንደሚያመራ በመረጃ ሰረተኞቻቸው አማካኝነት የዕለት ተዕለት መረጃ እንደሚያገኙ ግልፅ ነው ።

ለጥቅማቸው የሚረዳቸውን ውሳኔ ለመውሰድ የሚያበቃቸውን መረጃ ማግኘታቸው እሙን ነው። የዐረብ ፀደይ (The Arab Spring ) ዓይነት መጥቶ መስቅልቅሉን ከማውጣቱ በፊትና የአካባቢውም ፀጥታና መርጋጋት ወደ ማይፈልጉት አቅጣጫ ከማምራቱ በፊት ፤ ብርቅርቅ ለውጥ መጥቶ የሕዝቡን ዐመፅ ማለዘብ ይሻሉ። ለዚኽ ዘዴ ማስፈፀሚያ ከዐብይ አህመድ ዐሊ የተሻለ ተዋናኝ የለም ብለውም ያስባሉ። የሕዝቡን ዐመጽ ፍጥነት ለመቀንስ አደናቃፊ ጉቶ ይተክላሉ። በዚሕም ፋታ የሚገኝ ይመስላቸዋል ።

ከእንግዲኽ ወዲያ፤ የወያኔን ጠቃሚነት እምብዛም እንደሆነ ሳይገነዘቡት አልቀሩም ማለት አይቻልም ። በፈረሰኛ ውሃ ሙላት ውስጥ ፈርስ ለመቀይር ይሞክራሉ። ሌላ አዲስ ታማኝ ካገኙ ፤ከወያኔ ጋር ያላቸውን ቁርባን ቢያፈርሱ ደንታ የሚኖራቸው አይሆንም። ለዘላቂ ጥቅማቸው እንጅ፤ ለጊዜያዊ ወዳጅም የሚጨነቁበት ኅሊና የሚኖራቸው አይሆንም። የነርሱን የልተቆጠበ ድጋፍ፤ ለሌላ አዲስ ፈረሳቸው ከሰጡት፤ ወያኔ እንደ ዋንጫ መቀመጫ አውልቀው ከመጣል ወደ ኋላ አይሉም አይባልም ።

ትላንት ሎንዶን ላይ የአካሄዱትን ድራማ ዓይነት ፤ ከ 27 ዓመት በኋላ ዛሬ አዲስ አበባ ላይ ለመድገም የሚያግዳቸው ሊኖር አይችልም ቢባል ስህተት አይደለም። በዚያም ተባለ በዚህ፤ በእኛ በኩል ምን የጠበቅብናል ? የሚለውን ጥያቄ ለማስተናገድ በኃሳብ ደረጃ የሚከተሉትን መልዕክቶች ማስተላለፍ እንሻለን ።

- **1ኛ .** የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ የወያኔ ባላሥልጣናት ሹም-ሽር ሳይሆን ፤የሥርዓት ለውጥ ነው። መሠረታዊ ለወጥ ካልመጣ፤ትግሉ ትጠናክሮ ይቀጥላል እንጅ አይቆምም። ለቀጣይነቱም፤ ወያኔን ተጻርሮ የቆመው ኃይል ሁሉ፤ ከሕዝብ ጎን ተሰልፎ ሀገራዊ ትግሉን መቀጠል ይኖርበታል።
- **2ኛ.** " ዐብይ ዐህመድ ዐሊ ተወዳድሮ በከፍተኛ ድምፅ ተመርጦ የመጣ ነው " የሚለው የወያኔ ድራማ ተውኔት ፕሮፓጋንዳ ነው። በወያኔ ጓዳ የተወሸቁት ገንደ-ጥሮች፤ ከወያኔ መሪዎች በተሰጣቸው መመሪያ እጅና እግሩ ተኮድኩዶ እንዲመደብ የተደረገ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል ። ከነወሃት መሪዎች ይሁንታና ትዕዛዝ ውጭ አንዳችም ርምጃ ሊወስድ አይችልም።
- **3ኛ.** ይኸ ሹም ሽር ሁለት ፤ ዓላማዎችን ለማስፈጸም የታቀደ ነው።

  *ሀ.* የሕዝቡን ዐመፅ አቅጣጫ አስለውጦ ትግሉን ለማዳከም ፤

**ለ.** በኀወኃት ሡፈር የተፈጠረውን ሽብር አረጋግቶ ወያኔ ከድንጋጤው እንዲንሰራራ በማድረግ ሥልጣኑን እንዲያጠናክር ማድረግ ነው ።

- **4ኛ.** ከአንድ እስከ ሦስት ተራ ቁጥሮች የሰፈሩትን ሁኔታዎች በሚገባ ተገንዝበን፤ የግለሰቦች ሹም ሽር፤ የሕዝቡን ጥያቄ የማይመልስ መሆኑ ታውቆ፤ ትግሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከማደርግ ውጭ ሌላ አማራጭ አይኖርም ። **ምን ተይዞ ጉዞ ?**

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !